DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ይህ ደህንነቱ-የተጠበቀ እና አዎንታዊ-የሆነ/Positive ትምህርት ቤቶች ፖሊሲ (Safe and Positive Schools Policy)፤ ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲ፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና/ወይም መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

**ቻንስለሩ ያጸደቁት:** ______

**በስራ-ላይ መዋል የጀመረው:** ፌብሩዋሪ (February) 2 ቀን 2023

# ደህነቱ-የተጠበቀ እና አዎንታዊ/Positive የትምህርት ቤቶች ፖሊሲ

## I. ዓላማ እና የስፋት-መጠን (SCOPE)

የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)፣ ሁሉም ተማሪ የተወዳጅነት ስሜትን፣ ፈተና ተቋቋሚነት፣ እና አዎታዊ ተጽዕኖ ላለው ማህበረሰብ እና በሕይወት ስኬት-ለማበብ፣ ዝግጁ የሚሆኑበት-ዓለም እንዲሆን ነው። DCPS፣ አጠቃላይ ልጁ የሚያስፈልገውን ትምህርት - ጠንካራ-በሆነ፣ አስደሳች፣ እና ሁሉን-አሳታፊ የሆነ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና የቀለም-ትምህርት በሚሰጠው ተሞክሮዎች ውስጥ በመሳተፍ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ፤ ሁሉም ተማሪዎች ወደኮሌጅ እና የስራ-መስክ ዝጁነታቸውን ለማረጋገጥ በቁርጠኝነት-ይሰራል። ከዚህ-ቁርጠኝነት ጋር አንዱ-አካል በመሆን፤ DCPS ደህንነቱ-የተጠበቀ እና አዎንታዊ የሆነ የትምህርት ቤት አካባቢዎችን -ደህንነቱ-በተጠበቀ ሁኔታ እንዲገኝ-በማበረታታት ላይ ይሠራል። በሣይንስ ትምህርት እና የእድገት ሂደት መሠረት-በመያዝ፤ DCPS ተማሪዎ በማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና የቀለም ትምህርት ስኬት ላይ የሚያስፈልጋቸው ችሎታዎችን እንዲገነቡ እርዳታ-ከመስጠት ጋር በአንድነት - አዎንታዊ-የሆነ ግንኙነቶችን ቅድሚያ የሚሰጠው-ነገር ነው። ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት ማገድ፣ በመጨረሻነት የሚወሰድ-አማራጭ ነው፤ እና DCPS በምትኩ - ደረጃ-በደረጃ የሆነ የትምህርት ቤት ውስጥ ጣልቃ-ገብነት፣ እርዳታ እና ግንኙነትን በማድረግ - አዲስ እና አዎንታዊ የሆኑ የእርስ-በርስ ግንኙነት ማድረጊያ እና የመሳተፊያ መንገዶችን ለመፍጠር ያካሂዳል።

DCPS፣ በዓለም-አቀፍ አክብሮት-የመስጠት እና የነቃ፣ አዎንታዊ የሆነ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ችሎታዎችን ሊስተካከል የሚችል ልምዶችን- እንዲሁም፣ የተማሪዎችን የተለያዩ የቀለም-ትምህርት፣ ባህሪይ፣ እና ዕድገታዊ ፍላጎቶቻቸው ላይ - ደረጃ-ባለው እርዳታ-አሰጣጥ እና ጣልቃ-ገብነት ላይ መሠረት ያደረገ፤ ደህንነቱ የተጠበቀ እና አዎንታዊ የመማሪያ አካባቢዎች ለመፍጠር ይፈልጋል። የእያንዳንዱ ተማሪ ድምጾች ከፍ-ከፍ እንዲል ኃይል-የመስጠት፣ የወላጅን አስተያየትን የማነሳሳት፣ እና የሁሉንም ባለድርሻ-አባላቶች በአክብሮት የሚይዝ ሁሉን አካታች-እና ሁሉን ተቀባይ-የሆነ የትምህርት ቤት ማህበረሰብን በመንከባከብ፣ እንዲሁም - ቀለም-ያላቸው ተማሪዎች (students of color) ያካተተ ክስተቶች ላይ - ያልተመጣጠነ-ሂደቶችን መማጥፋት ላይ፤ የእኛ ዓላማ-ነው። DCPS፣ ፀረ-ዘረኝነት የትምህርት ቤት ዲስትሪክ እንዲሆን ስራውን ቀጥሎበት እየሰራ-ነው፣ ይህም ቀውስ-ሲከሰት ምላሽ የሚሰጥ እና ለሁሉም ልጅን-በተመለከተ ጎን-ለጎን ሆኖ ለሚቀርብ አቀማመጥ ላይ - የእያንዳንዱ የልጅ-የየግል ሁኔታን እና ሁሉን-አቀፍ በሆነ-ሁኔታ፣ ትምህርት-ሰጪዎችን የሚረዳ ነው።
ይህ በመካከላቸው ያለ የዕድል ክፍተት የሚፈጥሩ ነገሮችን፣ የተቋማትን የተዛባ አመለካከትን ለማስቆም፣ እና ለቀለም-ትምህርት እና ለማህበራዊ ስኬቶች እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች የሚያስወገድ - በተለይ-ደግሞ ቀለም-ባላቸው ተማሪዎች (students of color) መካከል - ይህን የሚያስወግድ አካባቢን የሚፈጥር-ነው። DCPS፤ የመለያየት-ልዩነቶች ጉልህ-በሆነ ሁኔታ በሚታዩባቸው - በታሪካዊነት ቀጥለው የሚገኙት-ላይ የበለጠ እርዳታዎችን በመስጠት፤ የማግኘት ዕድልን በመስጠት፣ አብሮ-መካተትን (inclusion)፣ እና ማረጋገጫን በመስጠት ላይ በንቃት-ለመስራት የሚገሰግስ ነው።

ይህ ፖሊሲ፣ ለተማሪ እርዳታዎች እና ባህሪያዊ ጣልቃ-ገብነቶችን፤ የማስተካከል ልምዶችን እና ባለ-በርካታ ዘርፍ የእርዳታዎች ዘዴን (Multi-Tiered System of Supports (MTSS)፣ የዲሲፕሊን ኮድ ጥሰቶችን እና ምላሽ-አሰጣጦችን፤ ወደ እገዳዎች ሊመራ-የሚችል በርካታ የስነ-ስርዓት ደረጃዎች ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ አጉል-ፀባዮችን ዓይነቶን ጨምሮ፣ ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ተማሪዎችን ዲሲፕሊን፣ በሂደት ላይ ያሉ ክንውኖችን፣ እና ለሠራተኞች በስልጠና እና በባለሞያተኛነት የእድገት ማሳደጊያ በኩል ለፖሊሲ ማስፈጸም የሚጠበቁባቸውን ሁሉ በመዋቅርነት አስቀምጦታል።

ይህ ፖሊሲ፣ ከዚህ ቀደም በዚህ በሚመለከተው ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲዎች፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

## II. ሥልጣን እና በስራ-ላይ የሚውል ሕግ (AUTHORITY AND APPLICABLE LAW)[1]

| **ምንጭ** | **ጥቅስ (Citation)** |
|---|---|
| የፌደራል ሕግ | - Individuals with Disabilities Education Act (IDEA), 20 U.S.C. § 1400 *et seq.*<br>- Gun-Free Schools Act, 20 U.S.C. § 7961 |
| የፌደራል ደንቦች | - IDEA implementing regulations, 34 C.F.R. § 300 *et seq.* |

[1] Nothing in this policy will supersede federal, state, or local law.

| | |
|---|---|
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት ሕግ | - የ1996፣ የጦር-መሣሪያዎችን ወደ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ያመጡ ተማሪዎች የማገድ ድንጋጌ፣ D.C. Official Code § 38-231 *et seq*.<br>- የ2018፣ የተማሪ የ'School Amendment'ን በአግባቡ-የማግኘት ድንጋጌ፣ D.C. Official Code § 38-236.01 *et seq*.<br>- የ2015፣ የPre-K ተማሪ የዲስፕሊን ማስተካከያ (Discipline Amendment) ድንጋጌ፣ D.C. Official Code § 38- 273.01<br>- የ2013፣ ትኩረት ያደረገ የተማሪ ውጤታማነት ማስተካከያ/Achievement Amendment ድንጋጌ፣ D.C. Official Code § 38-781 *et seq*. |
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች | የዲሲ የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (DC Office of State Superintendent of Education (OSSE)<br>- 5-A DCMR § 2103 – የቀሪዎች ጣልቃ-ገብነት (Absentee Intervention) እና በትምህርት ቤት መሠረት-ያደረገ የተማሪ እርዳታ ቡድኖች<br>- 5-A DCMR § 2199 – ትርጓሜ (Definitions)<br><br>የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)<br>- 5-B DCMR § 2103 – ያለማቋረጥ-መቅረት (Truancy)<br>- 5-B DCMR § 2200 – ሪፖርት ማድረግ<br>- 5-B DCMR § 2500 et seq. – የተማሪ ስነ-ስርዓት/Student Discipline (Chapter 25) |

## III. ቁልፍ-የሆኑ አባባሎች እና ትርጉሞች

**አካላዊ ጉዳት/Bodily injury** ማለት፤ በመቆረጥ፣ በመፋቅ/abrasion፣ በመቃጠል፣ ወይም ቅርጽን-በማጥፋት/disfigurement፤ አካላዊ ህመም፣ መታመም፣ የሰውነት አካልን ለማንቀሳቀስ አለመቻል፣ የኦርጋን ወይም የአዕምሮ ችግር፤ ወይም ማንኛውም ሌላ በሰውነት ላይ የሚደርስ ጉዳት፤ ምንም-ጊዜያዊ ቢሆንም-እንኳን። (D.C. Official Code § 38-236.01(1))

**የኮንትራት የደህንነት-ጥበቃ/Contract security** ማለት፤ በDCPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ - የደህንነት-ጥበቃ አገልግሎቶችን ለመስጠት ኮንትራክት-የወሰደ ከትምህርት-ቤቱ ውጪ የሆነ ኩባንያ ወይም ድርጅት። ኮንትራት የወሰደው ኩባንያ ተቀጣሪ-ሠራተኞች፤ በተመደቡበት ቦታቸው ውስጥ የደህንነት-ጥበቃ ሠራተኛ ሆነው ለማገልገል ፈቃድ-የተሰጣቸው እና ተልዕኮ ያላቸው፤ ስልጠና-ያላቸው ባለሙያተኞች ናቸው።

**በዲስፕሊን ምክንያት አለመመዝገብ/Disciplinary unenrollment** ማለት፣ ከትምህርት ቤት መባረር ወይም ሳይፈልጉ እንዲዘዋወሩ መደረግ። (D.C. Official Code § 38-236.01(3))

**በአስቸኳይ-ጊዜ እርምጃ መወገድ/Emergency removal** ማለት፣ ወዲያውኑ ከትምህርት ቤት ውጪ እንዲታገዱ የሚያደርግ፤ ወይም ተማሪው በትምህርት ቤት ውስጥ መገኘቱ - ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ለትምህርት ቤት ሠራተኞች - ወዲያውኑ ወይም በቀጣይነት አደጋ-ያመጣል ተብሎ በተገቢው-ሁኔታ የታመነበት በመሆኑ፣ በዲስፕሊን ምክንያት ተማሪውን ከምትህርት ቤት ውስጥ እንዳይመዘገብ የሚያደርግ። (D.C. Official Code § 38-236.01(4))

**ስሜታዊ ጭንቀት/Emotional distress** ማለት፣ የአዕምሮ ችግር ወይም ጭንቀት - ተራ-ከሆነ ሕክምና ወይም ካውንስሊንግ በላይ እርዳታ-የሚፈልግ። (D.C. Official Code § 38-236.01(5))

**ማግለል/Exclusion** ማለት፣ ተማሪውን ከዕለታዊ የክፍል የጊዜ-ሰሌዳ በዲስፒሊን ምክንያቶች ማስወገድ እና እገዳን ወይም በዲስፕሊን ምክንያት አለመመዝገብን የሚያካትት። (D.C. Official Code § 38-236.01(6))

**ማባረር/Expulsion** ማለት፣ በማንኛውም የ'DCPS' ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም ውስጥ - በሁሉም የክፍሎች እና የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍን ጨምሮ - የDCPS አማራጭ ትምህርታዊ አቀመመጦች ካልሆኑ በስተቀር - ለአንድ (1) የቀን-መቁጠሪያ ዓመት - ተማሪው ለመማር ያለውን መብት-የሚከለክል ነው። (D.C. Official Code § 38-236.01(5); 5-B DCMR § 2599.2)

**የግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized education program (IEP)** ማለት፣ ከጉዳተኝነት ጋር ለሚገኝ ለእያንዳንዱ ልጅ - በእድገት-ላይ ምልከታ የተደረገ፣ የታየ፣ ዳግም-ማስተካከያውን፣ ከወላጅ ጋር እና ከትምህርት ቤት ቡድኑ ጋር በስብሰባ ውስጥ የተደረገውን - የጽሁፍ መግለጫ ነው። 'አይኢፒዎች (IEPs)'፤ በአሁኑ-ጊዜ ያለው የክንውን ደረጃዎች ያካተተ መግለጫ-የሆነ፣ የልጁ ጉዳተኝነት እንዴት ትምህርቱ-ላይ ተጽዕኖ እንደሚያደርግ፣ ዓመታዊ ግቦች እና አላማዎችን፣ እና የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የጽሁፍ-መግለጫን የያዘ፣ ማመቻቻዎች/accommodations፣ እና ከጉዳተኝነት ጋር ለሚገኘው ልጅ ልዩ የሆነው ትምህርታዊ ፍላጎቶቹ ላይ አስፈላጊ-የሆኑ ማስተካከያዎችን፤ በsection 614(d) of IDEA (20 U.S.C. § 1414(d)) አስፈላጊ-በሆነው መሠረት አካትቶ-የያዘ ነው። (D.C. Official Code § 38-2601.02)

**የትምህርት ቤት-ውስጥ እገዳ/In-school suspension** ማለት - ተማሪው፣ የስነ-ስርዓት ቅጣትን በተከተለ ምክንያት፣ ከትምህርት ቤት መደበኛ የክፍል ጊዜ ሰሌዳ በጊዜያዊነት እንዲወጣ ተደርጎ፣ ከተማሪው ጋር በአካል በአንድ-ቦታ ላይ አብሮ ከሚሆን የትምህርት ቤት ሠራተኛ የቁጥጥር-ጥበቃ ስር ሆኖ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እንዲቆይ ሲደረግ። (D.C. Official Code § 38-236.01(8))

**ካለፈቃድ መለቀቅ/Involuntary dismissal** ማለት፣ በስነ-ስርዓት ምክንያቶች የተነሳ - በትምህርት ገበታ-ላይ ከተገኙበት ግማሽ (½) በሆነው የትምህርት ቀን - ከትምህርት ቤት እንዲወገድ ሲደረግ፤ በዚህ-ጊዜ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ሠራተኛው ቁጥጥር-ስር ያልሆነ እና በትምህርት ቤት ቅጥር-ግቢዎች ውስጥም ለማሆን የማይፈቀድለት ይሆናል። (D.C. Official Code § 38-236.01(9))

**ካለፈቃድ መዛወር/Involuntary transfer** ማለት፣ በስነ-ስርዓት ምክንያቶች የተነሳ - የተማሪው ተመዝግቦበት ከነበረው የDCPS ትምህርት ቤት - ለቀሪው የትምህርት ዓመት፣ ወይም ከዚያ-ወዲያ፣ ምዝገባው-ሲሰረዝ እና ተማሪው የሌላ የ'DCPS' ትምህርት ቤት ምዝገባ ነው። (D.C. Official Code § 38-236.01(10))

**ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ/Out-of-school suspension** ማለት፣ በስነ-ስርዓት ምክንያቶች የተነሳ - በትምህርት ገበታ-ላይ ከሚገኝበት ወደ ሌላ አቀማመጥ ተማሪው በጊዜያዊነት እንዲወገድ ሲደረግ፤ በዚህ-ጊዜ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ሠራተኛው ቁጥጥር-ስር ያልሆነ እና በትምህርት ቤት ቅጥር-ግቢዎች ውስጥም ለማሆን የማይፈቀድለት ይሆናል። የ"ከትምህርት ቤት እገዳ/out-of-school suspension" አባባል፤ ካለፈቃድ መለቀቅ/involuntary dismissalን ያካትታል። ከጉዳተኝነት ጋር ለሚገኙ ተማሪዎች (students with disabilities)፤ ይህ አባባል የሆነው - "out-of-school suspension"፤ መወገዱ የሚከናወነው፤ ምንም የየግል የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (Individualized Family Service Plan (IFSP) ወይም የ'IEP' አገልግሎቶች የተሰጡ-ከሌሉ፤ በእገዳው ከአስር (10) ቀናቶች ወይም ከዚያ ያነሰ በመሆኑ ምክንያት፤ ወይም መወገዱ ቢኖርም፤ ተማሪው በ'IFSP' ወይም 'IEP'ው መሠረት አገልግሎቶቹን ማግኘት የሚቀጥል ከሆነ-ነው። (D.C. Official Code § 38-236.01(13))

**ወላጅ (Parent)** ማለት፤ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ሌላ ሰው - በተማሪው ላይ የማሳደግ-ኃላፊነት ወይም ተማሪውን የመቆጣጠር ኃላፊነት-ያለው ነው። (D.C. Official Code § 38-236.01(14))

**ደህንነት/Safe** ማለት፤ ጥበቃ-የተደረገለት ወይም ለአደጋዎች ወይም አስጊ-ነገሮች ያልተጋለጠ፤ ጉዳት ወይም ጥፋት ያለመድረስ-ሁኔታ ማለት ነው። (D.C. Official Code § 5-132.01)

**የትምህርት ቤት ሪሶርስ ኦፊሰር (School resource officer)** ማለት፣ ማህላ-የገባ የሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ (Metropolitan Police Department (MPD) ሹም የሆነ፤ ለDCPS ወይም የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች - ከDCPS, የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች እና የማህበረሰብ-መሠረት ካላቸው ድርጅቶች ጋር በጋራ-ትብብር ለመስራት በሚል-ዓላማ፣ የDCPS ትምህርት ቤቶችን፣ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶችን፣ እና ስፍራ-ቦታዎቻቸውን - ለተማሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ እና ሠራተኞች - ደህና-ሆነው የተጠበቁ አካባቢዎች መሆናቸውን ለማረጋገጥ፤ የባህላዊ-ይዘት ባለው፣ ለዕድገት-ተገቢ የሆነ እና ማህበረሰቡን ያገናዘበ የፖሊስ-ጥበቃ አገልግሎትን ጥቅም-የማዋል ስልቶችን እና ልምዶችን የሚጠቀሙ ናቸው። (D.C. Official Code § 5-132.01)

**ማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርት (Social-emotional learning (SEL)** ማለት፤ ልጆች እና አዋቂዎች - ስሜቶችን ለመቆጣጠር እና ለመረዳት አስፈላጊ የሆኑትን - እውቀትን፣ አመለካከት፣ እና ችሎታዎችን በተሳካ-ሁኔታ የሚጠቀሙበት፤ አዎንታዊ-የሆኑ ግቦችን የሚያስቀምጡ እና ውጤታማ-የሚሆኑበት፤ ለሌሎች ሃዘኔታ የሚያሳዩ እና የሚሰማቸው፣ አዎንታዊ-የሆነ ግንኙነቶችን መፍጠርና መገንባት የሚችሉ እና ተግባራዊ-የሆነ ውሳኔዎችን₂ የማድረግ-ሂደትን ማካሄድ ነው።

**ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኝ ተማሪ/Student with a disability** ማለት፤ በsection 602(3) ስር - የ'Individuals with Disabilities Education Act (118 Stat. (118 Stat. 2652; 20 U.S.C. § 1401(3)) ወይም በ'Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973' ስር በሚገኘው-መሠረት - ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኝ ልጅ ተብሎ ብቁነቱ-የተሰጠው። (D.C. Official Code § 38-236.01(18) ተመልከቱ)

**እገዳ/Suspension** ማለት፤ በትምህርት-ቤት ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት -ውጪ (out-of-school) የሆነ እገዳ/suspension። (D.C. Official Code § 38-236.01(19))

**የጦር-መሣሪያ/Weapon** ማለት፤ አካላዊ-ጉዳት፣ አደጋ፣ ወይም ሞትን በሌላ ግለሰብ ላይ ለማድረግ ጥቅም-ላይ የሚውል ማንኛውም ዕቃ/object።

## IV. መስፈርቶች

### A. የሠራተኛ ስልጠና እና የሙያ-ስልጠና

ደህንነቱ-የተጠበቀ እና አዎንታዊ-የሆነ/positive አካባቢን - ለማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም-ትምህርት መማሪያ እና እድገትን ለመደገፍ እንዲያስችል፤ ሁሉም የDCPS ትምህርት ቤቶች - በትምህርት ቤት ላይ መሠረት ያደረጉ - ሦስት (3) ባህላዊ-ቡድንን መርጦ-መለየት ያለበት፤ ወይም የልጁን ሙሉ የማገገሚያ ልምዶችን፣ የቃላት-ማረጋጊያን የሚያደርጉ፣ ማህበራዊ-ስሜታዊነት መማር (social-emotional learning (SEL)ን፣ እና የማንጓጠጥ (bullying) መከላከል ላይ - ለማስፈጸም የሚችሉ ተጨማሪ ሠራተኞች ስልጠና-እንዲያገኙ ማድረግ አለበት። የባህል ዲን (Dean of Culture)፣ የማገገሚያ ልምምዶች አስተባባሪ (Restorative Practices Coordinator)፣ የ'In-Suspension' አስተባባሪ፣ ወይም የባህሪይ ቴክኒሺያን - እነዚህ የስራ-ቦታዎች[3] ትምህርት ቤቱ ካለው - በትምህርት ቤት ውስጥ መሠረት ያደረገ የባህል ቡድን - መሆን-አለበት።

የDCPS ማዕከላዊ የተማሪ ባህሪይ አገልግሎቶች እና የትምህርት ቤት ባህል እና አኳሃን ቡድን (Central Services Student Behavior and School Culture and Climate Team)፤ ስልጠናዎችን - ዒላማ-ለተደረጉ ተገቢ-የሆኑ አድማጮች - በትምህርት ቤት መሠረት ያደረጉ የባህል ቡድኖችን፣ በትምህርት ቤት መሠረት ያደረጉ ሠራተኞች፣ የማንጓጠጥ መከላከል ዋና-የግንኙነት ክፍል ሠራተኞች (points of contact (POCs)፣ የ'in-school suspension' አስተባባሪዎች፣ እና የኮንትራክት የጥበቃ-ሰራተኞችን ለሆኑ ይሰጣል። የተማሪ ባህሪይ እና የማገገሚያና ወደነበረበት የመመለስ ልምምዶች የባለሙያተኛነት ማሳደጊያ ስልጠናዎች፣ በሚከተሉት ርዕሶች ላይ ያካተተ ክፍለ-ጊዜዎችን የሚያካትቱ-ይሆናል:

- የተማሪ ባህሪይ መከታተያ (Student Behavior Tracker (SBT)፣
- ማንጓጠጥን (Bullying) መከላከል ስልጠና፣
- ወደነበረበት-የመመለስ ልምምዶች ተከታታይ-ክፍል፣
- የ'In-School Suspension' በድጋሚ-መመልከት፣
- የደህንነት-ጥበቃ እንክብካቤ (በቃላት ችግሮችን-ማብረድ እና መግታት)፣ እና
- የሙሉ የልጁን ዕድገት/የአዕምሮ-ሣይንስ (Brain Science)።

ሁሉም ስልጠናዎች፤ ከ'In-School Suspension' በድጋሚ-መመልከት' በስተቀረ፤ በትምህርት ቤት-ላይ መሠረት ላደረጉ - የባህል ቡድን አባላቶች የሚያስፈልጉ-ናቸው።

የሠራተኞቹ - በስልጠና ኮርሶቹ ውስጥ መካፈላቸው ቁጥጥር-የሚደረግበት፤ በዚህ-ስልጠና ውስጥ ተሳትፎ ተገቢነትን ለማረጋገጥ - በመፈረሚያ ወረቀት ወይም በኤሌክትሮኒክ - በማረጋገጥ-ይከናወናል። ትምህርት ቤቶችም፤ የደህንነት-ጥበቃ ፕሮቶኮሎችን በህንፃዎቻቸው ዙሪያ የሚያሳይ ምልክትን በመለጠፍ፣ የሙያ-ስልጠና ትምህርቶችን ለማጠናከር እና ተማሪዎችን ተገቢ-የሆነ እና የሚጠበቅባቸውን ባህሪይን ለማስታወስ የሚረዳቸው-ይሆናል።

---

[2] District of Columbia Public Schools, *About the DCPS Panorama Surveys*, available at [https://dcps.dc.gov/sites/default/files/dc/sites/dcps/page_content/attachments/About-the-Panorama-Surveys.pdf](https://dcps.dc.gov/sites/default/files/dc/sites/dcps/page_content/attachments/About-the-Panorama-Surveys.pdf).

[3] Schools are able to hire staff to best support their students and communities, and so may not all have the same staff positions.

### B. ማህበራዊ እና ስሜታዊ ጣልቃ-ገብነቶች እና እርዳታዎች

ትምህርት ቤቶች፤ ለመማር እና ማበራዊ-ስሜታዊነት ዕድገት አመቺ-የሆኑ እና፣ የጋራ-አክብሮች እና ትብብርን በሁሉም አባላቶች-መካከል ለሚገኙ የትምህርት ቤት ማህበረሰቡ[4] የሚያቀርብ - የደህንነት-ጥበቃ ያለው እና አዎንታዊ-የሆነ አካበቢዎችን የሚጠብቁ፣ የሚገነቡ እና የሚያረጋግጡ-ናቸው። ተማሪዎች ጭንቀት-ሲሰማቸው፣ አስቸጋሪና-ፈታኝ የሆነን ባህሪያቶችን በትምህርት ቤታቸው ወይም በመማሪያ-ክፍል ማህበረሰባቸው ውስጥ ሊያሳዩ ይችላሉ። ተማሪዎች የደህንነት እና እገዛ-ያገኙ መሆናቸው ስሜት ሲኖራቸው፣ ሲታወቅላቸው እና ሲሰሙ፤ አስቸጋሪና-ፈታኝ የሆኑ ባህሪያቶችን የማሳየት ሁኔታቸው በጣም-የቀነሰ-ይሆናል። DCPS፤ በትምህርት ቤቶች እና በመማሪያ-ክፍሎች ውስጥ ስኬታማ የሚያደርጋቸው ችሎታዎች እና የሚጠበቁባቸውን-ነገሮች - ተማሪዎች እንዲማሩ በመርዳት በቁርጠኝነት-ይሠራል። ተማሪው በመማሪያ አካባቢው ውስጥ፣ ተገቢ-ባለሆነ ወይም በሚረብሽ የባህሪይ ሁኔታ ውስጥ በሚሳተፍ ጊዜ፤ ትምህርት ቤቶች ለዚህ ባህሪይ ምላሽ የሚሰጡት - አዎንታዊ የሆነ አካባቢን የሚጠብቅ እና የማስተማር-መማር ሂደቱን የሚደግፈውን ለእድገታዊ ተገቢ የሆኑ ችሎታዎችን ለመገንባት የተቀረጹ ጣልቃ-ገብነቶችን በመጠቀም-ምላሽ የሚስጡ ይሆናል። የመከላከል ስልቶች - በማንኛውም በሚቻልበት ጊዜ፤[5] ሁሉ ጥቅም-ላይ መዋል አለበት፣ እና ጣልቃ-ገብነቶች - እንደ መልሶ-ማቋቋሚያ፣ ማስተካከያ፣ እና ትምህርታዊነት መሆን ያለባቸው እና ከመማሪያ ክፍል እና በትምህርት ቤት መገለልን-መቀነስ የሚያስችሉ-መሆን አለባቸው።

ተማሪዎችን በቀውስ-ምላሽ አሰጣጥ መነጽር አማካኝነት እየተመለከቱ መርዳት፤ ለዚህ የባህሪያዊ ጣልቃ-ገብነቶች ስርዓት - ቁልፍ-የሆነው ክፍል ነው። አስተማሪዎች፣ በስሜት ቀውስ-ሰጭ (trauma-responsive) የሆነ የመማሪያ አካባቢ ውስጥ እንዴት ማገዝ እንደሚችሉ የተካተቱት ምሳሌዎች፡ አስተማሪዎች አዎንታዊ እና የማረጋገጫ አነጋገሮችን በየዕለቱ መጠቀም፣ በእድገታዊ ሁኔታ ተገቢ-የሆነ፣ ወጥነት-ያለው፣ እና ሊተነበይ-የሚችል የመማሪያ አካባቢዎችን መፍጠር፣ ራስን ለመቆጣጠር ( self-management) የሚያግዙ ምንጮችን (resources) ማቅረብ፣ በግ ንኙነት ላይ ዕምነትን መገንባት እንዲችሉ ጊዜ መስጠት፣ እና የማስተማር፣ ሞዴል የማድረግና የትምህርት ቤት አቀፍ ባሕሪ የሚጠበቁትን እንደገና ማጠናከር ናቸው። የተማሪ ባሪይን ምላሽ-ለመስጠት ጥቅም-ላይ የዋሉ ተጨማሪ የጣልቃ-ገብነት እና እርዳታዎች ምሳሌዎችን ለማግኘት፤ በ'Appendix A' ላይ ተመልከቱ።

በተጨማሪነት - ደህንነቱ-የተጠበቀ እና አዎንታዊ-የሆነ ትምህርት ቤቶችን ለመፍጠር እና ተገቢ-የሆነ የተማሪ ባህሪይን ለመደገፍ፤ DCPS የሚከተሉትን መልሶ-ወደነበረበት-የመመለስ ልምምዶች ያጸድቃል እና የባለ-በርካታ ዘርፍ የእርዳታዎች ዘዴ (Multi-Tiered System of Supports (MTSS)ን በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ ያስፈጽማል።

#### 1. ወደነበረበት-የመመለስ ልምምዶች

መልሶ-ወደነበረበት የመመለስ ልምምዶች፤ በግለሰቦች በሌሎች ላይ የተፈጠረን ጉዳት በመጠገን እና ግንኙነቶችን መልሶ-በማስተካከል - ማህበረሰብን ለመገንባት፣ ግጭትን ለመቆጣጠር፣ እና ውጥረትን ለማስወገድ፤ DCPS በሚጠቀምበት ስልቶች ጥላ-ስር የሚገኝ፣ የማስታረቅ ጽንሰ-ሃሳቦች ናቸው። መልሶ-ወደነበረበት የመመለስ ልምምዶች[6] የሚያካትተው፤ ከተደረገው በደል ቀደም-ብሎ ጥቅም-ላይ የሚውል መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ሂደቶችን እና ግጭትን እና በደልን ለመከላከል - በንቃት-የሚሰራ ግንኙነቶችን መገንባት እና የማህበረሰባዊነት ስሜት እንዲኖር ማስፈለግን መጠቀም ያካትታል። መልሶ-ወደነበረበት የመመለስ ልምምዶች ላይ - የDCPS አቀራረቡ፤ ግንኙነቶችን እና የትምህርት ቤት ባህሎችን በአዎንታዊ-ሁኔታ በመገንባት ላይ በንቃት-መስራትን ይጠቀማል። በተጨማሪም፤ መልሶ-ወደነበረበት የመመለስ ልምምዶች፣ ለተጎዱት አካላቶች እንደ አማራጭ ሆኖ በቀረበ መንገድ እና፣ እነዚህን በአጉል-ባህሪያት የተጎዱ አካላትን - ከሌላ ሰው ጋር ፊት-ለፊት ሆነው መጋፈጥን እንዳይኖርባቸው በጭራሽ በማያደርግ ሁኔታ፤ እንደ ግጭትን ማስወገጃ አንዱ-አካል ሆኖ - ጥቅም-ላይ ሊውል ይችላል።

የመልሶ-ወደነበረበት የመመለስ ልምምዶች፣ ጠንካራ-ጎኖች እና ግንኙነቶችን መጠገኛ-መንገዶች፤ የሚያውኩ ባህሪይን መቀነስ፣ አስቸጋሪና-ፈታኝ ሁኔታዎችን ማብረድ፣ እገዳዎችን/suspensions መቀነስ፣ እና ማህበራዊ ግንኙነቶችን ማሻሻል ናቸው። የረጅም-ጊዜ ጥረቶች የሆኑት የመልሶ-ወደነበረበት የመመለስ ልምምዶች፤ የቀለም-ትምህርትን፣ የተማሪ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘትን፣ እና አዎንታዊ-የሆነ የትምህርት ቤት አካባቢን በመፍጠር - ለማሻሻል ያስችላል። ወደነበረበት-የመመለስ ልምምዶች ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፤ እባካችሁ እዚህ ተመልከቱ፤ https://dcps.dc.gov/page/restorative-practices።

---

[4] 5-B DCMR § 2500.1.

[5] 5-B DCMR § 2500.4.

[6] DCPS does not engage in restorative justice in its schools. Restorative justice is a reactive approach that consists of formal or informal responses to crime and other wrongdoing after it occurs.

2. ባለ-በርካታ ዘርፍ የእርዳታዎች ዘዴ (Multi-Tiered System of Supports (MTSS)

ለተማሪ የቀለም ትምህርት እና ማህበራዊ-ስሜታዊ እድገት አስፈላጊ የሆኑ - በትምህርት ቤት ያሉትን ባህሎችን እና አካባቢዎችን በበለጠ ለመንከባከብ፤ ሁሉም የ'DCPS' ትምህርት ቤቶች - 'MTSS'ን በጥቅም-ላይ ያውላሉ። 'MTSS'፣ ለትምህርት ቤቶች - በጥቅሉ የተማሪዎችን እና የአዋቂዎችን ፍላጎቶች እና ጠንካራ-ጎኖች ለመረዳት፤ መዋቅርን ያቀርባል። ጎን-ለጎን ሆኖ የሚሰራ ዘርፍ-ያለው እርዳታዎችን እና ጣልቃ-ገብነቶችን - በየግለሰቡ ጠንካራ-ጎችኖች ላይ ጥቅም-ላይ የሚውል እና በሚያስፈልገው-ነገር ዝሪያዎች እርዳታን የሚሰጥ-ነው። 'MTSS'፣ ስፋን-የሰደደው በሣይንስ መማር እና እድገት ላይ እና፣ የተማሪዎችን የተለያየ የባህሪያዊ እና የዕድገታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት የተቀረጸ-ነው። 'MTSS'፤ የDCPS ሙሉ-የሆነ ልጅ ተግባራዊነት ላይ የሚረዳ፣ ሁኔታዎችን-በማመቻቸት ለተማሪ ስኬትን እንዲያስገኝ በፀረ-ዘረኝነት ላይ ትኩረት ማድረግ፣ ስለ ተማሪዎች ንግግርና-ውይይቶችን ሁሉን-ባቀፈ ሁኔታ ማስተናገድ፣ እና በመረጃ-ስብስብ (data) የተመሠረተ እርዳታዎችን እና ጣልቃ-ገብነቶችን በመጠቀም - ችሎታዎችን እና የአዕምሮ-አስተሳሰቦችን ለተማሪዎች በመጠን-በመከፋፈል ለመጠቀም-ይረዳል።

MTSS@DCPS፤ በሦስት ዘርፎች ያሉት እርዳታዎች የተመሠረተ-ነው:

- **የ'Tier 1' እርዳታዎች** ለሁሉም ተማሪዎች - የባለቤትነት ስሜት እና ሰፊ-የሆነ የትምህርት-አሰጣጥ ልምዶችን ለማበረታታት፤ የንቃት እና የመከላከል እገዛዎችን የሚሰጡ፤
- **የ'Tier 2' እርዳታዎች** አነስተኛ ቡድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን - የዓለም-አቀፍ እርዳታዎች (ማለትም ዘርፍ/Tier 1) ፍላጎቶቻቸውን ሊያሟሉላቸው በማይችሉ-ጊዜ፤ ጠንካራ-ጎኖችን እና ፍላጎቶቻቸውን ለመርዳት የተቀረጸ ዒላማ-ያደረገ እርምጃዎች ናቸው፤ እና
- **የ'Tier 3' እርዳታዎች** ለአንድ ተማሪ በየግል-ሆኖ ጠንከር-ብሎ የተዘጋጀ እርዳታ ሲሆን፣ የበለጠ ጉልህ-ከሆኑ ፍላጎቶች ጋር ወይም እነዚህ ፍላጎቶች በዘርፍ (Tier) 2 እገዛዎች ሊሟሉ ያልቻሉ ናቸው።

የዓለም-አቀፍ ዘርፍ (Tier) 1 ልምዶችን ለሁሉም ተማሪዎች ጥቅም-ላይ በማዋል አማካኝነት፣ ዒላማ-የተደረገውን የዘር (Tier 2 እና 3 ጣልቃ-ገብነቶችን ተጨማሪ እርዳታ ለሚፈልጉ ተማሪዎች በመስጠት፤ የDCPSን ሌላ የባህሪያዊ ጣልቃ-ገብነት ስልቶችን እና እርዳታዎችን በአዎንታዊ የተማሪ ባህሪይ እና ደህንነት-ጥበቃ እና አጋዥ-በሆነ የትምህርት ቤት አካባቢዎች - ላይ 'MTSS@DCPS'፣ አብሮ-የሚሄድለት ሆኖ አግኝቶታል። በMTSS@DCPS ላይ - ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፤ እባካችሁ በDCPS_MTSS@k12.dc.gov ላይ ኢሜል አድርጋችሁ አነጋግሩን።

### C. ለዲስፕሊናዊ ጣልቃ-ገብነቶችን ከግምት-ውስጥ ማስገባት

በጣልቃ-ገብነቶች እና በዲስፕሊን ላይ የሚደረጉ-ውሳኔዎች፤ የየግል ተማሪዎችን እና ሠራተኞችን የሚያከብር፣ የትምህርት ቤት ማህበረሰቡን ፍላጎቶች የሚያመዛዝን፣ እና የቀለም-ትምህርት[7] መስተጓጎልን የሚቀንስ ነው። ሠራተኞች፣ በሂደት-ላይ እያደገ-የሚገኝን የዲስፕሊን ምላሾችን ማስፈጸም፣ ከተፈቀደው የዲስፕሊን ምላሾች መካከል - ተማሪዎች በተሳካ-ሁኔታ እራሳቸውን እንዲያስተካክሉ ዕድል ለመስጠት-ሲባል፣ ከዝቅተኛና ተገቢ-ከሆነው ምላሽ በመጀመር ያስፈጽማሉ። የዲስፕሊናዊ እርምጃ መሠረቶች የሆኑት እና የባህሪይ ዘርፎች/tiers እና ምላሾች፤ በ'Appendix B'[8] ውስጥ ተዘርዝረዋል። ጣልቃ-ገብነቶች እና ምላሾች ፍትሃዊ እና ወጥነት-ያላቸው፣[9] ምክንያታዊ/logical፣ ተገቢ፣ እና ትምህርት-ሰጪ የሚሆኑ፣ እና የሚከተሉትን መሰል-እውነታዎችን ከግምት-ውስጥ ያስገባሉ:

- የጥሰቱን ባህሪይ (The nature of the infraction)፤
- ከጥሰቱ-ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሁኔታዎች፤
- የተማሪው ዕድሜ፤
- የተማሪውን አጠቃላይ የማህበራዊ እና ስሜታዊ ይዞቶች (ለምሳሌ፤ ከዚህ-ቀደም የነበረው ባህሪይ፣ የቀውስ-መፈጠር ታሪክ ከነበረው፤ ማንኛውም የአዕምሮ ጤናን - ከግምት-ውስጥ የገባ-መሆኑን)፤
- ከዚህ-ቀደም በካውንስሊንግ ወይም ግጭትን ማስወገድ ጥረቶች ውስጥ ተሳትፎ-የነበረ መሆኑን፣ እንደ - የእኩዮች ሽልምግና ወይም ወደነበረበት-የመመለስ ልምምዶች፤
- ጉዳት/injury ደርሷል/አልደረሰም፤
- የጦር-መሣሪያ ወይም ቁጥጥር-ያለው አደንዛዥ ዕፅ በዚህ ውስጥ ነበረ/ወይስ አልነበረም፤
- የሌሎች ተማሪዎች እና ሠራተኞች የደህንነት-ጥበቃ፤
- የሌሎች ተማሪዎች የትምህርታዊ-አገልግሎት ፍላጎቶች፤

---

[7] 5-B DCMR § 2500.7.
[8] 5-B DCMR § 2500.11.
[9] 5-B DCMR § 2500.8.

- በትምህርታዊ-አሰጣጥ ውስጥ ለተማሪው ዲስፕሊን-እንዲደረግ የማስፈለግን-ሁኔታ፤ በየግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP) ወይም 'Section 504 plan' ውስጥ የተዘረዘሩትን ጨምሮ፤ እና
- ሁኔታዎችን ሙሉ-ለሙሉ የመረዳት-ሁኔታ።[10]

### D. *ተፈፃሚነት* (Applicability)

ይህ ፖሊሲ፣ በትምህርት ቤት ባለስልጣናት - እንደሚከተሉት፣ ተግባራዊ-ይሆናል:

- ተማሪው በትምህርት ቤት ግቢዎች ውስጥ በሚሆን-ጊዜ፤
- ተማሪዎች በትምህርት ቤት ግቢዎች ውስጥ ወይም ውጪ - በማንኛውም ክንውን ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ በሚማሩ ውወይም በሚሳተፉ ጊዜ፤ በመስክ-ጉዞዎች/field trips፣ የክፍል ጉዞዎች፣ ከትምህርት ውጪ በሆኑ (extracurricular) እንቅስቃሴዎች፣ ወይም በአትሌቲክ ውድድሮችን ጨምሮ - በDCPS ስፖንሰርነት ወይም ድጋፍ-ሰጪነት የሚካሄዱ ውስጥ፤
- ተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤት ግቢዎች ውጪ በሚሆኑ ጊዜ እና በDCPS ወይም በዲሲ የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education (OSSE) በቀረበ-መጓጓዣ በሚጓዙ-ጊዜ፣ እና በዚህ እንቅስቃሴ ወቅት ፖሊሲው በሚከለክለውን-በማንኛውም ባህሪይ ውስጥ በሚሳተፉ-ጊዜ፤
- ተማሪው በተከለከሉ በደል-ማከናወን ድርጊት ላይ፣ በትምህርት ቤቱ የፕሮግራም-አሰጣጥ ወቅት፣ ከትምህርት ቤት በፊት ወይም ከትምህርት ቤት በኋላ በሚደርግ-ጊዜ፤ እና
- ከትምህርት ቤት ግቢዎች ውጪ ወይም ከመደበኛ የትምህርት ሰዓታት ውጪ ጉልህ-በሆነ የትምህርት ቤት አካባቢው[11] ላይ መስተጓጎን በሚፈጥር - የተከለከለ የበደል-ድርጊት ውስጥ ተማሪው-በሚሳተፍ ጊዜ። ይህ ምናልባት የሳይበር-ማንጓጠጥ (cyberbullying)ን - ይህን በኤሌክትሮኒክ ዲቫይሶች አማካኝነት የሚተላለፉ ግንኙነቶችን ሊያካትት የሚችል እና፣ የማህበራዊ ሚዲያ እና ሌላ-ወደፊት ሊፈጠሩ የሚችሉ አፕሊኬሽኖች (applications) የኤሌክትሮኒክ ግንኙነት-ማደረጊያ ሆነው ከግምት-ውስጥ የሚገቡትን መጥቀምን ሊያካትት-ይችላል።

### E. *እገዳዎች* (Suspensions) *እና መወገድ* (Expulsion)

1. የቅድመ-ልጅነት ትምህርት (Early Childhood Education (ECE) (ማለትም፤ የቅድመ-መዋዕለሕፃናት (Pre-K))

DCPS፤ ሁሉንም በPre-K የመማሪያ-ክፍሎቻችን ውስጥ የሚማሩትን ታዳጊ-ተማሪዎቻችንን - የሚቀበል-ነው። አንዳንድ የ'ECE' ተማሪዎች አስቸጋሪና-ፈታኝ የሆኑ ባህሪያቶችን በትምህርት ቤት ውስጥ የሚያሳዩ ሊሆኑ-የሚችሉ ሲሆን፣ የልጅ ዕድገት ምርምር (child development research)[12] - ድጋፍ-ሰጪ የሆነ እና ለዕድገታዊ-ሂደት ተገቢ-የሆነ የመማሪያ ክፍል አካባቢን ማቅረብ - የልጆችን የማህበራዊ-ስሜታዊ እድገትን ለማበረታታት እና ልጆች ጠቃሚ-የሆነ እራስን የመቆጣጠር ችሎታዎችን ለማዳበር እንደሚረዳቸው ሃሳብ-አቅርቧል። ምርምር (Research) በተጨማሪም - በማስታወሻነት-ያቀረበው፤ በዚህ ዕድሜ ላይ ላሉ ልጆች እገዳዎች (suspensions) ወይም ማስወገድ (expulsions) - ውጤት-ሊያስገኝ የማይችል ስልቶች እንደሆኑ እና በልጆቹ ባህሪይ ላይ አዎንታዊ-ለውጥን ለማስገኘት የሚያስችል-እንዳልሆነ አሳስቧል። በተጨማሪም፤ እገዳዎች (suspensions) ልጆች ከሚያገኙ ወሳኝ-የሆነ የመማር ተሞክሩ የሚያግዳቸው ሲሆን፤ አብዛኛውን ጊዜ በመማሪያ-ክፍል ውስጥ መሆን በጣም የሚያስፈልጋቸውን ልጆች ሲጎዳ፣ እና በቤተሰብ እና በትምህርት ቤቶች መካከል ባለው ግንኙነት ላይ - ከፍተኛ ጫና የሚያደርግ-ነው።

---

[10] 5-B DCMR § 2500.9.
[11] 5-B DCMR § 2501.1.
[12] Early Learning Network, *Emerging Theme: Teacher-Child Relationships*, available at https://earlylearningnetwork.unl.edu/2019/05/20/teacher-child-relationships/; PennState Extension, *Interactions Matter: What Research Says and What You Can Do!*, available at https://extension.psu.edu/programs/betterkidcare/news/2016/interactions-matter; Center on the Social and Emotional Foundations for Early Learning, *Promoting Children's Success: Building Relationships and Creating Supportive Environments – Building Positive Relationships with Young Children*, available at http://csefel.vanderbilt.edu/modules/module1/handout5.html.

a. በእገዳዎች (Suspensions) እና ማስወገድ (Expulsions) ላይ - ክልከላ/Prohibition

በዲሲ ሕግ እና ደንቦች (D.C. law and regulations) ተከትሎ-ለመስራት እና በተገቢው-ሁኔታ ታዳጊ-ልጆችን ለመርዳት እና ለማሳተፍ፤ **የቅድመ-ልጅነት/early childhood (ማለትም፤ Pre-K) ተማሪዎች - ለማንኛውም የጊዜ እርዝመት፣**[13] **ሊወገዱ (suspended-ሊደረጉ አይገባቸውም።** ይህ፤ ሁለቱንም - በትምህርት ቤት ውስጥ እና ከትምህርት-ቤት ውጪ (Out-of-School) እገዳዎችን - የሚያካትት-ነው። **የቅድመ-ልጅነት ተማሪዎች (Early childhood students)፣ *በማንኛውምምክንያት* - ከትምህርት ቤት መወገድ (expelled-መደረግም) *ሊይችሉም፡*** በ'ECE እገዳዎች/suspensions' ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ እባካችሁ - የቅድመ-ልጅነት ትምህርት ክፍል (Early Childhood Education Division (ECED)ን በ DCPS.EarlyChildhood@k12.dc.gov. አነጋግሩ።

b. ከመማሪያ-ክፍል ውስጥ በጊዜያዊነት መወገድ

የ'ECE' ተማሪው ከመማሪያ-ክፍሉ ለጊዜያዊነት መወገድ በሚያስፈልግበት ጊዜ - እንደ ባህሪያዊ ጣልቃ-ገብነት ወይም እርዳታ አንዱ-አካል ሆኖ፤ ጊዜያዎ-መወገዱ ለተራዘመ-የጊዜ ወቅት ሊሆን የማይገባው እና ከግማሽ-ቀን መብለጥ የለበትም። ማንኛውም ከመማሪያ-ክፍሉ በጊዜያዊ-መወገድ፣ በ'SBT' ውስጥ በሰነድነት መመዝገብ አለበት።

ከመማሪያ-ክፍሉ ዕረፍት-መውሰድ የሚያስፈልጋቸው የ'ECE' ተማሪዎች፤ ደህነቱ-በተጠበቀ ቦታ ላይ ብቁ-በሆነ እና እርዳታ-ሰጪ አዋቂ-ሰው ክትትል-እየተደረገላቸው - እንደ የእርዳታ-ሰጪ ሠራተኞች፣ የትምህርት ቤት የስነልቦና ባለሞያ፣ ወይም የትምህርት ቤት መሪ ባሉት-እየተጠበቅ ሊቆይ-ይችላል። እያንዳንዱ ተማሪ እና የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ልዩ-የሆነ (unique) ነው - እና ተገቢ የሆነ እርዳታ-ሰጪ አዋቂ-ሰው ለእያንዳንዱ ሁኔታ ሊለያይ-ይችል ይሆናል። የትምህርት ቤት የጥበቃ ሠራተኞች፣ ፖሊስ፣ ወይም ሌላ የደህንነት-ጥበቃ ሠራተኞች - እንደ አዋቂ-ሆነው - ለልጁ እንዲረጋጋ ጊዜ ለመስጠት፣ ከልጁ ጋር አዎንታዊ የሆነ የየግል ግንኙነት ከሌላቸው በስተቀረ - ለማገልገል ብቁ-**አይሆኑም**።

c. የቤተሰብ እርዳታ

የ'ECE' ተማሪው ላሳየው ተገቢ-ያልሆነ ባህሪይ ምላሽ-ለመስጠት ሲባል - ወላጅ/አሳዳጊን ማነጋገር አስፈላጊ በሚሆኑበት ሁኔታዎች ውስጥ፤ ልጃዎቸ ለቀሪው የትምህርት ቀን ወደ ቤታቸው ለመውሰድ - ወላጅ/አሳዳጊ ሊወስኑ-ይችላሉ። ይህ ሊሆንና ከግምት-ውስጥ ሊገባ የሚችለው፤ ወላጅ/አሳዳጊ ጥያቄውን ካቀረቡ እና የትምህርት ቤት አስተዳዳሩ - ውጤት-አምጪ ስልት ነው ብሎ ከተስማማበት ብቻ ነው። **ትምህርት ቤቶች፤ ወላጅ፣ ልጁን ወደ መኖሪያ-ቤት በመውሰደ ላይ ምክር-*ላይሰጥ* ይችል-ይሆናል።** እነዚህ-ሁኔታዎች በሚፈጠሩ ጊዜ፤ ሁሉም ከዚህ-ቀደም የተደረጉት ጣልቃ-ገብነቶች እና ምላሾች - በ'SBT' ውስጥ በሰነድነት-የተመዘገቡ መሆን አለባቸው። **ይህ ቅጣት-የማያስከትል እርምጃ (non-punitive action) እና እገዳ (suspension) ያልሆነ መሆኑን፤ ትምህርት ቤቱ፣ ለልጁ-ወላጅ በጽሁፍ ማሳወቅ እና ግንኙነት/communicate ማድረግ-አለበት።** በሚቀጥለው-የትምህርት ቀን ልጁ ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ-ለመግባት ምንም እንቅፋት መኖር የለበትም (ማለትም፤ ወደ-ትምህርት ቤት ተመልሶ ከመግባቱ በፊት ምንም የወላጅ ስብሰባ ወይም ማንኛውም ሌላ እርምጃን መውሰድ አያስፈልግም)።

d. የተስተካከለ የጊዜ-ሰሌዳ

በአንዳንድ አልፎ-አልፎ በሚከሰቱ ሁኔታዎች ውስጥ፤ አጥሮ-የተቀነሰ የትምህርት ቀን (ማለትም፤ ግማሽ-ቀን) ድጋፍ-ሊሰጥ የሚችል እንደ የ'ECE' ባህሪይ ጣልቃ-ገብነት *ጊዜያዊ መፍትሄ* ሊሆን ይችል-ይሆናል። የተስተካከለ የጊዜ-ሰሌዳ - ከግምት-ውስጥ ሊገባ የሚችልበት ሁኔታ፤ ትምህርት ቤቱ እና ቤተሰብ፣ ውጤት-አስገኚ ስለመሆኑ ከተስማሙ- እና ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት አካባቢው ቀስ-በቀስ እንዲለማመድ ለመርዳት የጊዜ-ገደብ የተደረገለት ስልትን መቅረጽ አስፈላጊ በመሆኑ ላይ ከተስማሙ ብቻ-ነው። ሁሉም፣ ከዚህ-ቀደም የተደረጉት ጣልቃ-ገብነቶች እና ምላሾች - በ'SBT' ውስጥ በሰነድነት-የተመዘገቡ መሆን አለባቸው።

የተስተካከለ የጊዜ-ሰሌዳ - ከግምት-ውስጥ ከማስገባት በፊት፣ የትምህርት ቤት አመራሮች - 'ECED'ን እና የትምህርት ቤት የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ (Instructional Superintendent)ን - ማነጋገር አለባቸው። ይህ - ለልጁ የማስተማሪያ-እርምጃ የሆነ እና እገዳ (suspension) እንዳልሆነ፤ ትምህርት ቤቱ በጽሁፍ ለወላጅ/አሳዳጊ ማሳወቅ እና ግንኙነት/ communicate ማድረግ አለበት። ወላጅ/አሳዳጊ፣ በማንኛውም-ጊዜ - ወደ መደበኛ የትምህርት ቀኑን የጊዜ-ሰሌዳ በመቀጠል የማካሄድ መብት-አላቸው።

---

[13] *See* D.C. Official Code § 38–273.03, 5-B DCMR § 2500 *et seq*.

2. ከK-12 ክፍሎች:

በ'Chapter 25[14] የ'D.C. Municipal Regulations' በሆነው ውስጥ የተካተቱ ሁሉም መስፈርቶች፤ ከ' Student Fair Access Act' ጋር ግጭት-የማይፈጥሩና - የባህሪይ ጥሰቶችን ደረጃዎች የሚዘረዝረውን ዘርፎች (tiers) ጨምሮ፣ በስራ-ላይ ሆነው የሚቀጥሉ ናቸው። ስለ ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) ርዝመቶች እና በ'Student Fair Access Act' ላይ ስለሚፈጠር ተጽዕኖ - ቁልፍ መስፈርቶችን በተመልከተ በማጠቃለያ ሰንጠሮዦቹን፤ እባካችሁ በአባሪዎቹ/appendices ላይ ተመልከቱ።

a. ኢ-መደበኛ ማስወገድ (Informal Exclusion) ላይ ክልከላ/Prohibition

ለተማሪዎች በዲስፒሊናዊ ምክንያቶች ከዕለታዊ የትምህርት ቤት የጊዜ-ሰሌዳቸው መወገድን-የሚያስከቱ-ነገሮች ሁሉም፣ እንደ ከትምህርት ቤት መወገድ/exclusions ተብለው-የሚወሰዱ እና በዚህ-ሁኔታዎች ውስጥ - በዚህ ፖሊሲ ላይ የሚገኙት ሁሉ አስፈላጊ የሆኑ ክፍሎቹን መከተል ያስፈልጋል። ከK-12 ተማሪ የሆነ፤ ከትምህርት ቤት ህንፃ መወገድ እና ወደ ትምህርት ቤት ከመመለስ መከልከል የሌለበት መሆኑን፤ በዲስፒልናዊ ምክንያቶች ካለፍላጎት የተደረገ መለቀቆች/involuntary dismissals ጨምሮ፤ ተማሪው ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) ወይም በዲስፒሊን ምክንያት ስራ-አጥነት (disciplinary unenrollment)[15] ካልሆነ በስተቀረ፤ መወገድ-የለበትም። ከዚህ መስፈርት ጋር ተገዢነትን ለማረጋገጥ፣ ሁሉም ከትምህርት ቤት መወገዶች (exclusions) - በ'SBT' ውስጥ እንደ-ሰነድ ሆነው መመዝገብ አለባቸው።

b. ከመዋዕለሕፃናት እስከ 5ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች

(1) ከK-5 ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ (Out-of-School Suspension) ምክንያቶችን ላይ - የሚገድቡ-ነገሮች

ከK እስከ 5 ክፍሎች ውስጥ የሚገኝ-ተማሪ፤ ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ ( out-of-school suspension)ን ወይም በዲስፒሊን ምክንያት ለሚፈጠር ስራ-አጥነት (disciplinary unenrollment)፤ **ተማሪ - ሆን-ብሎ የፈጠረው፣ ለመፍጠር-የሞከረው፣ ወይም አካላዊ-ጉዳቶችን ለመፍጠር ማስፈራሪያዎችን-ያደረገ ወይም ስሜታዊ ጭንቀትን ለሌላ ሰው ላይ የፈጠረ መሆኑን፤ ከትምህርት ቤት ፖሊሲው ጋር ተስማሚ-በሆነ ሁኔታ - የትምህርት ቤት አስተዳደሩ ካልወሰነ-በስተቀረ፣** ከትምህርት ቤት ግቢው ውጪ ላይ[16] የተፈጠረውን ባህሪይ ጨምሮ፤ እገዳ አይሰጠውም። ይህን መከልከያ በዘርፍ/tiers የባህሪይ ጥሰቶች፤ ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) ሊያስከት-ስለመቻሉ፣ በተመለከተ ተግባራዊ ስለሚሆነው መመሪያ-በተመለከተ፤ በአባሪዎች/appendices መገኘት ይችላል።

(2) ከK-5 ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ (Out-of-School Suspension) ርዝመት ላይ፣ የሚገድቡ-ነገሮች

ከK እስከ 5 ክፍሎች ውስጥ የሚገኝ ተማሪ፣ በቀለም-ትምህርት ዓመቱ ውስጥ - በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ-በስተቀረ፤ ለማንኛውም የየግል ክስተት - **ከአምስት (5) ተከታታይ የትምህርት ቀናት** ላልበለጠ-ጊዜ ወይም ከ**ሃያ (20) የተጠራቀመ የትምህርት ቀናት** በላይ የሆነ፤ ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension)ን ማግኘት-የለበትም:

- ቻንስለሩ/The Chancellor፤ ለተማሪው እና ለወላጅ፤ ለምን ከ20-ቀን ገደብ የበለጠ ጊዜው፣ የዲስፒሊን እርምጃው ከሌላ አማራጭ ምላሾች የበለጠ ተገቢ-ሆኖ እንደተገኘ የሚገልጽ-የጽሁፍ ማረጋገጫ በማቅረብ፤ ወይም
- የተማሪው ጠባይ-የአስቸኳይ-ጊዜ የማስወገድ እርምጃን ለመውሰድ አስፈላጊነት የሰጠው እና፣ ለአስቸኳይ-ጊዜ መወገዱ (emergency removal) ማረጋገጫ ጽሁፍ - ለተማሪው እና ለወላጅ[17] በማቅረብ-ነው።

c. ከ6 እስከ 8ኛ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ፣ ተማሪዎች

(1) ከ6-8 ክፍል ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ (Out-of-School Suspension) ምክንያቶችን ላይ፣ የሚገድቡ-ነገሮች

ከ6 እስከ 8 ክፍሎች ውስጥ የሚገኝ-ተማሪ፤ ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ ( out-of-school suspension)ን ወይም በዲስፒሊን ምክንያት ለሚፈጠር ስራ-አጥነት (disciplinary unenrollment)፤ **ተማሪ - ሆን-ብሎ የፈጠረው፣ ለመፍጠር-የሞከረው፣ ወይም አካላዊ-ጉዳቶችን ለመፍጠር ማስፈራሪያዎችን-ያደረገ ወይም ስሜታዊ ጭንቀትን ለሌላ ሰው ላይ የፈጠረ መሆኑን፤ ከትምህርት ቤት ፖሊሲው ጋር ተስማሚ-በሆነ ሁኔታ - የትምህርት ቤት አስተዳደሩ ካልወሰነ-በስተቀረ፣ ከትምህርት ቤት ግቢው ውጪ ላይ[18] የተፈጠረውን ባህሪይ ጨምሮ፤ እገዳ አይሰጠውም። ይህን መከልከያ በዘርፍ/tiers የባህሪይ ጥሰቶች፤ ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) ሊያስከት-ስለመቻሉ፣ በተመለከተ ተግባራዊ ስለሚሆነው መመሪያ-በተመለከተ፤ በአባሪዎች/appendices መገኘት ይችላል።**

---

14 A current copy of Chapter 25 is available at: https://dcps.dc.gov/chapter25.

15 D.C. Official Code § 38-236.04(f).

16 D.C. Official Code § 38-236.04(a)(1).

17 D.C. Official Code § 38-236.04(b).

(2) ከ6-8 ክፍል ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ (Out-of-School Suspension) ርዝምት ላይ፣ የሚገድቡ-ነገሮች

ከ6 እስከ 8ኛ ክፍሎች ውስጥ የሚገኝ ተማሪ፣ በቀለም-ትምህርት ዓመቱ ውስጥ - በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ-በስተቀረ፤ ለማንኛውም የየግል ክስተት - ከ**አስር (10) ተከታታይ የትምህርት ቀናት** ላልበለጠ-ጊዜ ወይም ከ**ሃያ (20) የተጠራቀመ የትምህርት ቀናት** በላይ የሆነ፤ ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension)ን መጋለጥ-የለበትም:

- ቻንስለሩ/The Chancellor፤ ለተማሪው እና ለወላጅ፤ ለምን ከ20-ቀን ገደብ የበለጠ ጊዜው፣ የዲስፒሊን እርምጃው ከሌላ አማራጭ ምላሾች የበለጠ ተገቢ-ሆኖ እንደተገኘ የሚገልጽ-የጽሁፍ ማረጋገጫ በማቅረብ፤ ወይም
- የተማሪው ጠባይ-የአስቸኳይ-ጊዜ የማስወገድ እርምጃን ለመውሰድ አስፈላጊነት የሰጠው እና፣ ለአስቸኳይ-ጊዜ መወገዱ (emergency removal) ማረጋገጫ ጽሁፍ - ለተማሪው እና ለወላጅ[19] በማቅረብ-ነው።

d. ከ9 እስከ 12ኛ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ፣ ተማሪዎች

(1) ከ9-12 ክፍል ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ (Out-of-School Suspension) ምክንያቶችን ላይ፣ የሚገድቡ-ነገሮች

ከ9 እስከ 12ኛ ክፍሎች ውስጥ የሚገኝ፣ ተማሪ - ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ተማሪ ላይ የሚጠበቀው - ከግማሽ-በላይ ተማሪዎች - ከ18 ዓመት በላይ በሆኑበት ትምህርት ቤት ውስጥ፤ ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) ማግኘት-አይችልም፤ ወይም በሚከተሉት-ሁኔታ ለስራ-ማጣት የዲስፐሊን ሁኔታ አይዳረጉም:

- የDCPSን ወይም የትምህርት ቤት የአለባበስ ኮድን ወይም
የዩኒፎርም/uniform ህጎችን መጣስ፤
- ሆን-ብሎ እንቢተኝነትን ማሳየት፤ ወይም
- ከትምህርት ቤት ግቢዎች ውጪ እና እንደ በትምህርት ቤት-ስፖንሰር የተደረገ እንቅስቃሴ አካል ሳይሆን የተከሰተ ባህሪይ፤ ተማሪዎች - ሆን-ብለው የፈጠሩት፣ ለመፍጠር-የሞከሩት፣ ወይም አካላዊ-ጉዳቶችን ለመፍጠር ማስፈራሪያዎችን-ያደረጉ ወይም ስሜታዊ ጭንቀትን ለሌላ ሰው ላይ[20] ያልፈጠሩ-እስከሆኑ ድረስ።

(2) ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ (Out-of-School Suspension) ርዝመት ላይ፣ የሚገድቡ-ነገሮች

ከ9 እስከ 12ኛ ክፍሎች ውስጥ የሚገኝ፣ ተማሪዎች - ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ተማሪዎች ላይ የሚጠበቀው - ከግማሽ-በላይ ተማሪዎች - ከ18 ዓመት በላይ በሆኑበት ትምህርት ቤት ውስጥ፤ በቀለም-ትምህርት ዓመቱ ወቅት ከ**አስር (10) ተከታታይ የትምህርት ቀናት** ላልበለጠ-ጊዜ ወይም ከ**ሃያ (20) የተጠራቀመ የትምህርት ቀናት** በላይ የሆነ፤ ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension)ን ሊያስጠይቀው አይችልም።

- ቻንስለሩ/The Chancellor፤ ለተማሪው እና ለወላጅ፤ ለምን ከ20-ቀን ገደብ የበለጠ ጊዜው፣ የዲስፒሊን እርምጃው ከሌላ አማራጭ ምላሾች የበለጠ ተገቢ-ሆኖ እንደተገኘ የሚገልጽ-የጽሁፍ ማረጋገጫ በማቅረብ፤ ወይም
- የተማሪው ጠባይ-የአስቸኳይ-ጊዜ የማስወገድ እርምጃን ለመውሰድ አስፈላጊነት የሰጠው እና፣ ለአስቸኳይ-ጊዜ መወገዱ (emergency removal) ማረጋገጫ ጽሁፍ - ለተማሪው እና ለወላጅ[21] በማቅረብ-ነው።

---

18 D.C. Official Code § 38-236.04(a)(1).
19 D.C. Official Code § 38-236.04(b).
20 D.C. Official Code § 38-236.04(a)(2).
21 D.C. Official Code § 38-236.04(b).

e. ማባረር (Expulsion)

በ'Student Fair Access to Schools Act' ውስጥ የሚገኘው ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳዎች (out-of-school suspensions)ን መከልከያዎች፤ ለመወገድ (expulsions) - በስራ-ላይ አይውሉም። ለ'Tier V' ባህሪይዎች መወገድ (Expulsion)፣ ወይም የ'Gun-Free Schools Act' ጥሰቶች - በ'Chapter 25' ስር - የይግባኝ-አቤቱታ ሊቀርብ ይችል-ይሆናል።

የ'Gun-Free Schools Act'ን እና የ'D.C. Law' በመከተል፤ እና ከ'Individuals with Disabilities Education Act (IDEA) ጋር በተቀናጀ ሁኔታ፤ የጦር-መሣሪያ ወደ ትምህርት ቤት ያመጣ ማንኛውንም ተማሪ - DCPS ቢያንስ ለአንድ (1) ዓመት ያህል ማባረር/expel ማድረግ ያስፈልገዋል።[22] የ'Gun-Free Schools Act'ን በመጣስ የሚደረግ መወገድ - ምናልባት የአቤቱታ-ይግባኝ ሊቀርብ የሚችልበት-ሁኔታ የሚኖር እና፣ በቻንስለሩ-ብቻ ማስተካከያ ሊደረግለት-ይችላል።[23]

f. በአስቸኳይ-ጊዜ መወገዶች (Emergency Removals)

ተማሪው፤ እየተካሄደ ያለ ሂደት (due process) በሁሉ ገጽታዎች ላይ ከመጠናቀቃቸው በፊት፣ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ለአስቸኳይ-ጊዜ ሁኔታው አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ሆነው ከተገኙ፤ ከመደበኛ የትምህርታዊ-አሰጣጥ ቀኑ ወዲያውኑ ሊወገድ-ይችል ይሆናል።[24]

በአጠቃላይ የትምህርት አሰጣጥ ውስጥ ለሚገኝ ተማሪ፣ የአስቸኳይ-አደጋ ሁኔታ (emergency situation) - ወይ-በትምህርት ቤቱ ውስጥ ባለው አጠቃላይ-ሁኔታ ምክንያት (ለምሳሌ፤ ቁጥሩ-የጨመረ ድብድቦች ወይም አካላዊ-ጥቃቶች) ወይም-ደግሞ በዚህ ተማሪ ላይ የሚታየው ባህሪይ በጣም አዋኪ እና አደገኛ በመሆኑ ምክንያት - በጣም እውን-የሆነ እና ወዲያውኑ አስጊ የሆነ የጤና እና የደህንነት-ስጋትን በሌሎች የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላቶች ላይ ሊያደርስ በመቻሉ-ምክንያት - ወይም የትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ወይም ትምህርት ቤቱ ወይም ከፊል-አካሉ፤ በመደበኛ ክንውኖቹ ውስጥ መቀጠል የማያስችላቸው ከሆነ-ነው።[25]

ከ' IEP' ወይም የ '504 plan' ጋር የሚገኝ ተማሪ፣ ወይም እነዚህን-አገልግሎቶች ለማግኘት የተገመገመ ተማሪ፤ ከሚከተሉት መስፈርት ውስጥ ቢያንስ አንድ (1)ን የተማሪው ባህሪይ አሟልቶ መገኘት አለበት:

- ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ወይም ወደ ትምህርት ቤት ክንውኖች - የጦር-መሣሪያ ይዞ-መምጣት፤ ወይም
- በትምህርት ቤቱ ውስጥ - በትምህርት ቤት ግቢዎች ወይም በትምህርት ቤት ክንውኖች ሆነው በDCPS ስልጣን ስር በሚከናወኑትበት ጊዜ፤ ተማሪው፣ አደገኛ የሆነ አካላዊ ጉዳትን በሌላ ሰው ላይ - በማድረሱ።[26]

በሙሉም በአስቸኳይ-ጊዜ መወገዶች (emergency removal) በሚከሰቱ-ጊዜ:

የአስቸኳይ-ጊዜ መወገዱ (emergency removal)፤ ከ'Student Fair Access Act' ጋር ተገዢ መሆን ያለበት እና፣ ከK እስከ 8 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፤ **ተማሪው፣ ሆን-ብሎ የፈጠረው፣ ለመፍጠር-የሞከረው፣ ወይም አካላዊ-ጉዳቶችን ለመፍጠር ማስፈራሪያዎችን-ያደረገ ወይም ስሜታዊ ጭንቀትን ለሌላ ሰው ላይ የፈጠረ መሆኑን፤ ከትምህርት ቤት ፖሊሲው ጋር ተስማሚ-በሆነ ሁኔታ - የትምህርት ቤት አስተዳደሩ ካልወሰነ-በስተቀረ፣** ከትምህርት ቤት ግቢዎች ውጪ[27] የተፈጠሩትን ባህሪይ ጨምሮ፤ ተማሪዎች - የአስቸኳይ-ጊዜ መወገድን እንዲያገኙ ሊያደርግ-አይችልም፤ እና

- ቻንስለሩ፣ ወይም ተወካያቸው፤ ለአስቸኳይ-ጊዜ መወገዱ ማረጋገጫ-ማብራሪያ የሚሰጥ ጽሁፍን - ለተማሪው እና ወላጅ ማቅረብ አለበት።[28]

g. መቅረቶች/Absences እና አርፍዶ መድረስ/Late Arrivals

ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ካልሆኑ-በስተቀረ፤ በትምህርት ቤት ውስጥ ከግማሽ-በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ በሆኑበት ትምህርት ቤት ውስጥ፤ ተማሪው፣ በፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች ወይም አርፍዶ ወደ ትምህርት ቤት በመድረስ-ምክንያት - ተማሪው ከምዝገባው ለመሰረቅ የሚያስችለውን ከሃያ (20) ወይም ከዚያ በላይ ተከታታይ የሙሉ-ቀን ከትምህርት ቤት ካለፈቃድ መቅረቶች[29] ካልኖሩት በስተቀረ - ከትምህርት ቤት ውጪ ለሆነ እገዳ (out-of-school suspension) ወይም የዲሲፕሊን ከቅጥር-መገለል (disciplinary unenrollment)ን -ሊያገኝ-አይችልም።

---

[22] 20 U.S.C. § 4141(a); D.C. Official Code § 38-231.
[23] D.C. Official Code § 38-231; 5-B DCMR § 2505 *et seq*.
[24] 5-B DCMR § 2504.4.
[25] 5-B DCMR § 2504.4.
[26] 5-B DCMR § 2510.5(b).
[27] D.C. Official Code § 38-236.04(a)(1).
[28] *See* D.C. Official Code § 38-236.04(b)(3)(B).

h. የቀለም-ትምህርት ስራ (Academic Work)ን የማግኘት እና ክሬዲት ማግኘት (Earn Credit)ን፣ በእገዳው ወቅት - የማግኘት መብት

ለእገዳ (suspension) የተጋለጠ ተማሪ፣ ተገቢ-የሆነው የቀለም-ትምህርት ስራውን ለማጠናቀቅ ወይም ክሬዲት/credit ለማግኘት እና ወደ ሌላ-ክፍል ለማለፍ ወይም ለምርቃት የሚያስፈልግን ስራ የማግኘት-መብቱን በእገዳው (suspension) ወቅት ከማግኘት ሊከለከል-አይችልም።30 በተጨማሪም፤ ለማንኛውም እገዳ ለተደረገበት ተማሪ - የየግል ተማሪን ፍላጎቶችን ለማሟላት ያለውን ዕቅድ የትምህርት ማስተካከያን በማድረግ መቀጠልን ጨምሮ - እንደየ-አስፈላጊነቱ፤ የተማሪውን ወደ መማሪያክፍል መመለስን ሊያግዙ-የሚችሉትን የትምህርት ዕቅድን መቀጠል አለበት። ዕቅዱ፤ ከትምህርት ቤት ውጪ በሆነበት-ጊዜ፣ ተማሪው በትምህርት-ቤት ስራው ላይ መቀጠሉን ለማረጋገጥ - ተገቢ የሆነ እርምጃዎችን ያካታተ-ሆኖ፤ ስለ ማንኛውም ትምህርት ቤት ስራው፣ ተማሪው እገዳ-ተደርጎበት በነበረበት ወቅት ላይ ሊጠናቀቅ-ያልቻለ የትምህርት ቤት ስራን ማጠናቀቂያ ተጨማሪ-ጊዜ (make up ማድረጊያን) ጨምሮ - ከትምህርት ቤት ሠራተኞች ጋር መነጋገር/communicate ማድረግ-አለበት።31

i. በእገዳ/Suspension ወይም መወገድ/Expulsion ወቅት የሚደረግ ተሣትፎ

እገዳ-የተደረገባቸው ወይም እንዲወገዱ የተደረጉ ተማሪዎች፤ በማንኛውም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴው ውስጥ - በእገዳው ወይም በመወገዱ ጊዜያቸው ወቅት ውስጥ ለመካፈል ብቁ-አይሆኑም። ሊፈቀድላቸው የሚችለው ነገር ቢኖር፤ በቻንስለሩ ወይም በቻንስለሩ ተወካይ አማካኝነት-ፈቃድ ያገኘ፣ ለ'system-wide testing'፣ ወይም የ'College Board' ወይም የመግቢያ ፈተናዎች/admission examinations ለመውሰድ-ብቻ ሊፈቀድላቸው ይችል-ይሆናል።32

j. ወደ ትምህርት ቤት መመለስ

ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ (out-of-school suspension)ን አጠናቅቆ የሚመለስ-ተማሪ፤ በሚመለስበት ቀን - ከተማሪው ጋር ወላጅ መምጣት፣ በኮንፈረንስ መሳተፍ፣ ወይም በሌላ-ሁኔታ በትምህርት ቤት መገኘትን-ላይ ተመርኩዞ መከናውን አያስፈልገውም።33

## F. ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ተማሪዎች እና ዲስፕሊን

ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኝን ተማሪ ማግለል (exclusion)ን በተመለከተ - በ'Americans with Disabilities Act (ADA)' እና በ'IDEA' ሕጎች መሠረት፣ ትምህርት ቤቶች ልዩ የሆነ ምልከታ-ማድረጊያ መውሰድ-አለባቸው።34 ትምህርት ቤቶች፤ ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኘው ልጅ - የልዩ ትምህርት (special education) እና የዲስፕሊናዊ መዝገቦች፣ የመጨረሻ-ውሳኔዎችን በዲስፕሊናዊ እርምጃ ላይ ለሚወስደው ሰው(ዎች) መታራቱን እና ከግምት-ውስጥ ገብቶ መታየቱን ማረጋገጥ-አለባቸው። ይህን መሰል ሰነዳዊ-አቀራረብ ሊያካትት የሚችለው፣ ነገር-ግን በዚህ ብቻ-ሣይወሰን፤ የተማሪውን በአሁኑ-ጊዜ ያለውን 'IEP'፣ የዲሲፕሊን ፋይል፣ ተጠራቅሞ-የተቀመጠ ፋይል፣ እና ሪፖርቶች ወይም ከጤና ወይም የአዕምሮ ጤና ሐኪሞች35 የተሰጡ-ሃሳቦች።

---

29 D.C. Official Code § 38-236.04(c). Please note that all such unenrollments must done in compliance with the DCPS Attendance & Truancy Policy, available at https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies.
30 D.C. Official Code § 38-236.04(d).
31 D.C. Official Code § 38-236.03(b)(4).
32 5-B DCMR § 2504.6.
33 D.C. Official Code § 38-236.04(e).
34 D.C. Official Code § 38-236.05; 20 U.S.C. § 1415(k); 34 C.F.R §§ 300.530-536; 5-B DCMR § 2510.
35 *See* 5-B DCMR § 2510.2.

1. ከትምህርት ቤት ለመታገድ ውሳኔው-ማድረግ ምልከታዎች (Manifestation Determination Reviews (MDR)

